በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

የ6ኛ ክፍል የመጀመሪያ መንፈቀ አመት ሞዴል ፈተና

አማርኛ, ታህሳስ 2015ዓ.ም/ JANUARY 2023G.C

የጥያቄ ብዛት: 40 **የተፈቀደው ሰዐት: - 1 ሰዐት**

አጠቃላይ ትዕዛዝ

ይህ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ነው። በዚህ ፈተና ውስጥ 40 ጥያቄዎች ተካተዋል፤ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሆነውን አማራጭ የያዘውን ፊደል በመመረጥ ለመልስ መስጫ በተሰጠው ወረቀት ላይ በመጥቆር መልስ ይሰጣል። በፈተና ላይ የተሰጡትን ትእዛዞች በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናውን መስራት ይጠበቅባችኋል። መልስ የሚሰጥው ከፈተናው ጋር በተያያዘው የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ነው ፤በመልስ መስጫው ላይ ትክክለኛውን መልስ የሚጠቆረው በእርሳስ ብቻ ነው፤ ትክክለኛው መልስ በማጥቆር ሲሰራ ለማጥቆር የተፈቀደው ቦታ በሙሉ በሚታይ መልኩ በደንብ መጥቆር አለበት፤ የጠቆረውን መልስ ለመቀየር ቢፈለግ በፊት የጠቆረውን በደንብ በማጥፋት መጽዳት አለበት።

ፈተናውን ሰረቶ ለመጨርስ የተፈቀደው ሰአት 1 ሰአት ነው። ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተሰጠው ሰዐት ሲያበቃ ለመስሪያነት የምንጠቀምበትን የመጻፊያ እርሳስ ማስቀመጥ እና ፈተናው መስራት ማቆም አለብን። ፈተናው እንዴት እንደሚሰበሰብ በፈታኙ/ኟ እስከሚነገር ድረስ በቦታችን ተቀምጠን መጠበቅ አለብን።

መኮረጅ ወይም በፈተና ሰአት የፈተናን ህግ የማያከብር ተፈታኝ ፈተናው አይያዝለትም፤ ፈተናውን እንዳይፈተንም ይደረጋል።

ፈተናውን መስራት ከመጀመራቹሁ በፊት በመልስ መስጫው ላይ መሞላት የሚገባውን መረጃ ሁሉ በጥንቃቄ መሞላት አለበት።

ፈተናውን መስራት ጀምሩ ሳይባል መጀመር አይፈቀድም !

መመሪያ አንድ፡- ከተራ ቁጥር 1-10 ያሉት ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ምንባብ ላይ የተመሰረቱ ናቸው ። ምንባቡን በጥሞና በማንበብ ለጥያቄዎቹ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል ሆነውን መልስ ምረጥ /ምረጪ።

አንድሬ ማልሮ

አንድሬ ማልሮ (1901-1976) የልቦለድ ደራሲ፣ የኪነጥበብ ፈላስፋና የማይበገር ታጋይ ነበር። በጉርምስናው ዘመን ወደ ካምቦዲያ ተጓዘ ። እዚያም ለመቶዎች አመታት ጫካ ውጧቸው ጠፍተው የነበሩ የጥንት ቤተመቅደሶችና ከተሞች እየተፈለጉ እየተገኙ ነበር ። ማልሮ በግሉ እዚህ ፍለጋ ውስጥ ገብቶ የአርኪኦሎጂ ቁፋሮ አካሂዶ ከቤተመቅደስ የተለያዩ ሀውልቶችና የተለያዩ የቅርስ እቃዎችን አገኘ ። ያገኘውን ሁሉ ለሃገሪቱ መንግስት አስረክቦ ወደ ሐገሩ ገባ ። አንድሬ ማልሮ ወደ ቻይና ሔደ ። በ1927 የቻይና አብዮት ሲካሔድ በቅርብ አጥንቶና በድርጊት ተሳትፎ (የሰው ልጅ ሁኔታ) (L condition Humaine) የተባለ ታላቅ ልቦለድ ጻፈ ። ፍልስፍናና ድርጊት በደራሲውም በገጸ ባህሪያቱም ውስጥ ተወራራሽ ናቸው ።

የፅስፓኝ የእርስ በእርስ ጦርነት ተነሳ ። ማልሮ ወደ ዚያ ዘመተ ፣ ፋሺስቶችን ሊዋጋ ። እንደ ማልሮ አይነቶቹ ጦረኞች የአገርድን በር አይወስናቸውም ። የሪፐብሊካኑ ወገን አየር ኃይል ውስጥ አዛዥ ሆኖ ተዋጋ ። በ1940 ተማረ ከናታሰረ ። ከታሰረበት አመለጠ ነገር ግን የስፓኝ ሪፐብሊካኑ ወገን ድልሆነ ። ማልሮ ወደ ሃገሩ ፈረንሳይ ተመልሶ የነጻይቱ ፍራንስ ጦር ሃይል ውስጥ አዛዥ ሆኖ ጦርነቱን ቀጠለ ። ማልሮ እሩቅ ምስራቅን ስለሚወዳትና ስለሚያውቃት ለጀነራልደጎል ልዩ መልዕክተኛ እየሆነ ተመላልሶባታል።

ከ1958 እስከ 1968 ማልሮ በፕሬዝዳንት ደጎል መንግስት ውስጥ የባህል ጉዳይ ሚኒስተር ሆነ ለውቢቷ ፍራንስ ባህልት ልቅ የግንባታ አስተዋጽኦ አድርጓል ። በየክፍለ ሐገሩ የባህል ተቋማትና ሙዚየሞች አስከፍቷል ። (የዝምታ ድምጾች) (Less Voix du Silence) የሚል ትልቅ መጽሃፍ በመጻፍ ስነጥበብን በስፋትና በጥልቀት በመተንተን በዘመኑ አንባቢዎች ከፍተኛ ተወዳጅነትን አትርፏል ።

(ሰብሀት ገብረ እግዚአብሄር፣እነሆ ጀግና፣2009፣193-194፣ በመጠኑ ተሸሽሎ የተወሰደ)

1. አንድሬ ማልሮ በጉርምስናው ወቅት የተጓዘው የትነው?
   A. ቻይና C. ስፓኝ
   B. ካምቦድያ D. ፈረንሳይ
2. አንድሬ ማልሮ ተማርኮ የታሰረው መቼ ነበር?
   A. በ1968 C. በ1940
   B. በ1927 D. በ1958
3. ፕሬዝዳንት ደጎልየ የትሃገር ፕሬዝዳንት ነበሩ?
   A. የቻይና C. የስፓኝ
   B. የካምቦድያ D. የፈረንሳይ

4. ከላይ ቀረበው ምንባብ ምን አይነት ድርሰት ነው?
   A. ልቦለድ ድርሰት C. አፈታሪክ
   B. የግለሰብ የሂወት ታሪክ D. ተረት
5. በምንባቡ መሰረት ‹ድልሆነ›ሲል ምን ማለቱ ነው?
   A. አሸነፈ C. ተሸነፈ
   B. ሸሸ D. ተስማማ
6.በምንባቡ መሰረት ‹ታጋይ› ለሚለው ቃልፍቺ ሊሆን የሚችለው ------ ነው።
   A. ወታደር C. አማጺ
   B. ጉልበተኛ D. አርበኛ
7. በምንባቡ መሰረት አንድሬ ማልሮ ምን ያህል መጽሃፍትን ጻፈ?
   A. ሁለት C. አራት
   B. ሶስት D. አንድ
8. ምንባቡ በምን ያህል አንቀጾች የተዋቀረ ነው?
   A. ሁለት C. አምስት
   B. አራት D. አንድ
9. አንድሬ ማልሮ በስንት አመቱ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ?
   A. በአር ባሁለት C. በሰባ አምስት
   B. በሰባ ስድስት D. አሁንም በህይወት አለ
10.ባለታሪኩ አንድሬ ማልሮ የየት ሃገር ዜጋ ነው?
   A. የቻይና C. የስፓኝ
   B. የካምቦድያ D. የፈረንሳይ

መመሪያ ሁለት፡- ከተራ ቁጥር 11 እስከ 40 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል። እያንዳንዱን ጥያቄ በጥሞና በማንበብ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጪ።

11. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ ስለ አንቀጽ ትክክል የሆነው የቱ ነው?
   A. አንድ ሃሳብ ብቻ ይተላለፍበታል
   B. በርካታ ሃሳቦች ይተላለፉበታል
   C. ቃላት ተቀናጅተው የሚፈጥሩት የጽሁፍ መዋቅር ነው
   D. ሁሉም መልስ ናቸው

12. ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ ለተጸአ ስም ምሳሌ ሊሆን የሚችለው_____ነው።

   A. መምህር C. ተራራ
   B. ጨለማ D. ኢትዮጵያ

13. በጫካ ውስጥ በርካታ እንስሳት ይኖራሉ ። የተሰመረበት ቃል_____ነው።

   A. የተጸአስም C. ረቂቅስም
   B. የወልስም D. የነገርስም

14. ከዚህ በታች ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ ነጻ ምዕላድ የሆነው የቱነው?

A. መጣች
C. ትምህርት
B. ሃገራችን
D. ተራራማ

15. **አትሌቶቻችን** የሚለው ቃል በምዕላድ ተነጣጥሎ ሲጻፍ ትክክለኛ ቅርጹ _____ነው።

A. አትሌቶች- አችን
C. አትሌት- አቻችን
B. አትሌት-አች-አችን
D. አትሌት-አች-ኣች-ን

16. ከሚከተሉት ውስጥ የአንቀጽ ባህሪ ያልሆ ነው የትኛው አማራጭ ነው?

C. ነጠላ ውጤት
C. አጽኖት
D. አንድነት
D. ውህደት

17. ከሚከተሉት ሃሳቦች ውስጥ የቃላዊ ግጥም ጠቀሜታ የሆነው የቱ ነው?

A. ማንነትን መግለጽ
C. ሃዘንና ደስታን መግለጽ
B. ፍቅርና ጥላቻን መግለጽ
D. ሁለም የቃላዊ ግጥም ጠቀሜታ ናቸው

19. በጎምላላ በሬ ግፋ ሲል ግፋ ሲል
ቆርቆሮ ቤት ሰራ ፋኖስ የሚመስል ። ይህ ቃላዊ ግጥም የ_____ቃላዊ ግጥም ነው።

A. የፉከራ ቃላዊ ግጥም
C. የእርሻ ቃላዊ ግጥም
B.የሽለላ ቃላዊ ግጥም
D. የፍቅር ቃላዊ ግጥም

20. የአንድን ነገር አሰራር፣ አከዋወን ምስል ከሳች በሆነ መልኩ የሚያቀርብልን የድረሰት አጻጻፍ አይነት_____ነው።

A. አመዛዛኝ ድርሰት
C. ተራኪ ድርሰት
B. አወዳዳሪ ድርሰት
D. ገላጭ ድርሰት

21. አንድን ሁነት በጊዜ ቅደም ተከተል የሚያቀርብልን የድረሰት አጻጻፍ አይነት_____ ነው።

A. አመዛዛኝ ድርሰት
C. ተራኪ ድርሰት
B. አወዳዳሪ ድርሰት
D. ገላጭ ድርሰት

22.የህጻኑ ልጅ ለቅሶ የእናቱን አንጀት <u>በላ</u>። የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺ_____ነው።

A. ተመገበ
B.አሳዘነ
C. አሸነፈ
D. ሰረቀ

23. ተደሰተ ብለን አዘነ ካልን ጎበዘ ብለን ምን እንላለን?

A. በረታ
C. ጠነከረ
B. ተጋ
D. ሰነፈ

24. እንጀራውን ጋግረሽ ከማን ጋር በላሽው፣

ደረት የሚመታ_____፤

ይህን ቃላዊ ግጥም በክፍት ቦታው ገብቶ ሊያሟላው የሚችለው የቱ ነው?

A. ወዴት አደረሽው
B. ሎሚ የወረወርሽው
C. ጎረቤት ያጣሽው
D. ወሽማ ያመጣሽው

25. ሲያመኝ ውሎ ሲያመኝ ሊያድርነ ወይ፣

ይኸ ሰርቶ መብላት ጤና ላይሆንነ ውይ። ይህ ቃላ ዊግጥም_____ነው።

A. የፉከራ
B. የቀረርቶ
C. የሙሾ
D. የሰርግ

26. ከዋኙ ሲያቀርብ ተደራሲው ‹‹ እሺ... ከዚያስ....›› በሚል የሚቀርብ የስነቃል አይነት የትኛው ነው?

A. ተረት
B. እንቆቅልሽ
C. የልመናግጥም
D. የልጆችጨዋታ

27. በቀጣይ አመት የሰባተኛ ክፍል ተማሪ እሆናለሁ ። ይህ ዓ/ነገር የተጻፈው በ_____ ___ጊዜ ነው።

A. በአላፊ ገዜ
B. በአሁን ጊዜ
C. በትንቢት ጊዜ
D. ጊዜው አይታወቅም

28. እናቱ ከገበያ <u>አሁን</u> መጣች ። የተሰመረበት ቃል_____ነው።

A. የጊዜ ተውሳከ ግስ
B. የቦታ ተውሳከ ግስ
C. ሁኔታ ተውሳከ ግስ
D. የምክንያት ተውሳከ ግስ

29. ከሚከተሉት ስርዓተነ ጥቦች ውስጥ አዕሮተ ቃላትን ለመመስረት የምንጠቀምበት ነው ።

A. ነጠላ ሰረዝ
B. ህዝባር
C. ትዕምር ተጥቅስ
D. ነጠብጣብ

30. ከዚህ በታች ተዘበራርቀው የተቀመጡ ዓ/ነገሮች ተስተካክለው ሲጻፉ

ሀ. ትምህርት ቤት የሰልፍ ሰአት አልቆ ደረስኩኝ ።

ለ. ከእንቅልፌ አርፍጀ ተነሳሁ።

ሐ. ቁርሴን ሳልበላ ተጣድፌ ከቤት ወጣሁ።

መ. ርዕሰ መምህሩ አንበረከከኝ።

ሠ. ማታ ፊልም ሳይ አምሽቼ ተኛሁ ።

A. ሀ፣ለ፣ሐ፣መ፣ሠ
B. ሠ፣ሐ፣ለ፣መ፣ሀ
C. ሠ፣ለ፣ሐ፣ሀ፣መ
D. ሀ፣መ፣ለ፣ሠ፣ሐ

31. የአፍሪካ መዲና ናት አዲስ አበባ ። ይህ የሰዋሰው ስህተት ያለበት ዓ/ነገር ተስተካክሎ ሲፃፍ፣

A. አዲስ አበባ ናት የአፍሪካ መዲና ።
B. የአፍሪካ መዲና አዲስ አበባ ናት።
C. ናት የአፍሪካ መዲና አዲስ አበባ ።
D. አዲስ አበባ የአፍሪካ መዲና ናት ፡

32. አንበሳ ብለን ጎበዝ ካልን እርግብ ብለን_____እንላለን።

A. የዋህ
B. ጅል
C. ወፍ
D. ተንኮለኛ

33. የዘሬ አመት የ5ኛ ክፍል ተማሪ ነበርኩ ። ይህ ዓ/ነግር የተጻፈው በ _____ጊዜ ነው።

A. በትንቢት ጊዜ
B. በኃላፊ ጊዜ
C. በአሁን ጊዜ
D. መልስ አልተሰጠም

34. ፈተና እየተፈተንኩ ነው። ይህ አረፍተ ነገሮች የተጻፈው በ__ጊዜ ነው።

C. በትንቢት ጊዜ
D. በኃላፊ ጊዜ
C. በአሁን ጊዜ
D. መልስ አልተሰጠም

35. ወንድሜ ከደረጃ ላይ ወድቆ ክፉኛ ተጎዳ። የተሰመረበት ቃል የቃል ክፍሉ ምንድ ነው?

A. ስም
B. ቅጽል
C. መስተዋድድ
D. ተውሳከግስ

36. ኢክራም በርትታ ታጠናለች_____ፈተናውን ትደፍናለች ። በክፍት ቦታው የሚገባው አያያዥ ቃልየ ቱነው?

A. ነገርግን C. ስለዚህ
B. ይሁንእንጂ D. ሆኖም

37. **ኢ/ሴ/ህ/ን/ጽ/ቤት** ይህ በአፅሮተ ቃል የተጻፈ ጽሁፍ ተብራርቶ ሲጻፍ ከሚከተሉት ትክክል የሆነው የቱ ነው?

A. የኢትዮጵያ ሴቶች ህዝብ ጉባኤ ጽህፈ ትቤት
B. የኢትዮጵያሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ጽፈ ትቤት
C. የኢትዮጵያ እና ሴራሊዮን ህዝብ ግንኙነት ጽፈትቤት
D. የኢትየጵያ ሴቶች እና ህጻናት ግንኙነ ጽጽህፈ ትቤት

38. **የሃገራችንን** የሚለው ቃል በምዕላድ ተከፋፍሎ ሲጻፍ_____ነው።

A. ሃገር- ኣችን - ን C. የሃገር - ኣችን- ን
B. የ- ሃገር - ኣ - ችንን D. የ- ሃገር- ኣችን - ን

39. ከሚከተሉት ውስጥ የቃል ክፍሉ ቅጽል የሆነው የቱ ነው?

A. ልባም C. ክፉኛ
B. ጫካ D. ትናንት

40. ህጻኑ ልጅ ገና በለጋ እድሜው <u>ተቀጠፈ</u> ። የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺ ምንድ ነው?

A. ተቀነጠሰ C. ታመመ
B. ሞተ D. ተቆረጠ